2013

# የሐዋርያው ጳውሎስ መልእክት ወደ ፊልሞና

ለመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት የተዘጋጀ
የኢትዮጵያውያን ወንጌላዊት ባፕቲስት ቤ/ክ - ዳላስ
ቅዱሳንን የማጽናት አገልግሎት

Ethiopian Evangelical Baptist Church
2822 S Jupiter Rd, Garland TX 75041
www.wongelkedallas.org
www.eebc-dallas.org
Tel.2147030100
Fax: 2147030161

- “የቅዱሳን ልብ በአንተ ስራ ስለ ዐረፈ በፍቅርህ ብዙ ደስታና መጽናናትን አግኝ ቻለሁ”
- “በእስራቴ ስለ ወለድሁት ልጄ ስለ አናሲሞስ እለምንሃለሁ”
- “በአንዳች ነገር የበደለህ ቢኖር ግን ወይንም ብድር ቢኖርበት ይህን በእኔ ላይ ቁጠረው”
- “አስቀድሞ ስላልጠቀመህ አሁን ግን ለእኔም ለአንተም የሚጠቅም ሆኗል”
- “ከእንግዲ እንደ ባሪያ አይሆንም እንደ ተወደደ ወንድም አድርገህ ተቀበለው”

## የሐዋርያው ጳውሎስ መልእክት ወደ ፊልሞና
ጥናት አንድ

**መግቢያ**

**ጸሓፊው፡ የተጻፈበት ጊዜና ቦታ**

ሐዋርያው ጳውሎስ ይህን አጭር መልዕክት የጻፈው በሮም እስር ቤት ሆኖ የፊልጵስዮስን፣ የኤፌሶን፣ የቆላስይስን መልዕክቶች በጻፈበት(በ60)ዓ.ም ገደማ እንደሆነ ብዙዎች ያምናሉ። ይህንን የፊልሞናን መልዕክት ወደ ቆላስይስ የላከው በአናሲሞስና በቲኪቆስ እጅ እንደሆነ ይታወቃል ( ቆላ 4፡7-8)። ሐዋርያው ጳውሎስ ቆላስይስንና የፊልሞናን መልዕክቶች የጻፈው ኤፌሶን በነበረበት ጊዜ ነው የሚሉ ቢኖሩም በሌላ ወገን ግን በሮም እስር ቤት እያለ መጻፉን ብዙዎች የሚስማሙበት ሃሳብ ነው።

**ተደራሲው ፡ ( ተቀባዮች ) ዳራውና እና ዓላማው**

ሐዋርያው ጳውሎስ ይህን መልዕክት የጻፈው ከቆላስይስ ባሪያ አሳዳሪዎች አንዱ ለነበረው ፊልሞና ለሚባለው አማኝ ነው (ቆላ 4፡1 ጋር ያነጻጽሩ)። የባርያ አሳዳሪ ሥርዓት በአዲስ ኪዳን ምን እንደሚመስል (ቆላ 3፡22 የኤፌሶን 6፡5-9 ይመልከቱ)። በወቅቱ ፊልሞና በዛ ያሉ ባርያዎች እንደነበሩት ይገመታል። ከባርያዎቹ አንዱ አናሲሞስ ከአሳዳሪው ከፊልሞና ንብረት ሰርቆ ወደ ሮም እንደኮበለለ መጽሐፉ ያመለክታል(ከቁ 18-19 ይመልከቱት)። በዚሁ ምክንያት ከቤት ጠፍቶ የኮበለለ ይመስላል። በሮም ሕግ ይህ ዓይነት ወንጀልም በሞት የሚያስቀጣ ነበር። በሮም ከተማ አናሲሞስ ከሐዋርያው ጳውሎስ ጋር የመገናኘት ዕድል በማግኘቱ በእርሱ አገልግሎት ጌታን ተቀብሎ ክርስቲያን እንደሆነ ብዙዎች ይስማማሉ (ቁ 10 ይመልከቱ)። ከሐዋርያው ጳውሎስ ጋር ካደረጉት ውይይትና ምክክር በኋላም አናሲሞስ ወደ ቀድሞው አሳዳሪው (ጌታው) ለመመለስ ፈቃደኛ በመሆኑ ሐዋርያው ጳውሎስ አናሲሞስን እንደ ቀደመው በባርነት ሳይሆን እንደ ክርስቲያን ወንድም አድርጎ እንዲቀበለው ይህን የግል መልዕክት በመጻፍ ፊልሞናን በጉዳዩ ይማጠነዋል (ቁ16 ይመልከቱ)።

**አቀራረቡና ውቅሩ**

አናሲሞስን ለመቀበል ፊልሞና ፈቃዳኛ እንዲሆን ጳውሎስ በፍቅር፣በጥበብና በትሕትና መልእክቱን አለዝቦ ጽፎለታል (ቁ 11 በማንበብ ያገናዝቡ )። ለፊልሞና ያቀረበውን ልመና ጳውሎስ የጻፈው የጥንት ግሪክና የሮም ምሁራን ወይንም መምህራን ይህን አይነት ጽሑፍ የሚያዘጋጁበትን ዘዴ በመከተል እንደሆነ ይታወቃል። ይህም የፍቅር ግኙኝነትን ለመመስረት አስተሳሰብን ለማስቀየርና አንድን ሰው ለማሳመን የሚጻፍበትን ዘዴ ሲሆን በመንፈስ ቅዱስ መረዳትና ምሪት የተጻፈ እንደሆነም መዘንጋት የለበትም። አናሲሞስ የሚለውን ስም የጠቀሰው በእርሱና በፊልሞና መካከል ያለውን ፍቅርና ቅርርብ ከገለጠ በኋላ ሲሆን (ቁ 10 )ልመናውንም ያቀረበው በመልዕክቱ መጨረሻ አካባቢ (ቁ17) ላይ ነው። ይህ መልዕክት ለዚህ ጥናት እንዲሆን የተከፋፈለው ከቁ.1-8፣ከቁ.9-15 እና ሶስተኛው ከቁ.16-25 ይሆናል።

በቤተ ክርስቲያናችን የዚህ መልእክት ጥናት ዓላማ ሁላችንም እርስ በርስ ተቻችለን በፍቅር፣በይቅርታ፣ በትህትናና ሌሎችን ለአገልግሎት በማብቃት ህይወት በመመላለስ ጌታ እስኪመጣ ወይም እኛ ወደ እርሱ እስክንሄድ ድረስ ታግሰን መኖር እንዳለብን ለማሳሰብ ነው።

**መደምደሚያ**

የፊልሞና መልዕክት 25 ቁጥሮች ሲኖሩት ለሰው ዓይን የማይመች ከሚመስል ቦታ የተጻፈ አጭር መልዕክት ቢሆንም እንኳን ለክርስቲያኖች እጅግ አስፈላጊ የሆነ ዘላለማዊ መልዕክት አለው። የመልዕክቱ ማዕከላዊ ሀሳብ ይቅርታ ሲሆን አማኞች

በደለኞችና ኃጢአተኞች ቢሆኑም እግዚአብሔር ይቅር እንዳላቸው ሌሎችን ይቅር ማለት እንዳለባቸው በጥብቅ ያስተምራል። አናሲሞስ በይቅርታ ምክንያት ለራሱ ህይወትና ለወንጌል ሥራም የተረፈ ሰው ነው።

***የመወያያ ጥያቄዎች***

( ለዚህ ቀን ጥናት ከተመደበው ጊዜ ቀድማችሁ ጥናቱን ክጨረሳችሁ የቀረውን ጊዜ እንድትጸልዩ እናበረታታለን)

1. የመግቢያውን ሃሳብ በመመልከት በሚከተሉት ጥያቄዎች ዙሪያ ተወያዩ

ሀ. ስለ መልዕክቱ ጸሐፊ እና ስለ መልዕክቱ ተቀባይ

______________________________________________________________________________

ለ. ስለተጻፈበት ጊዜና ቦታ

______________________________________________________________________________

ሐ. ስለ መልዕክቱ ዓላማ ____________________________________________

2. በአዲስ ኪዳን የባሪያ አሳዳሪ ስርዓት ምን እንደሚመስል የኤፌሶን 6፡5-9 ቆላ3፡22 በማንበብ ተወያዩበት

_____________________________________________

3. ከዛሬው ጥናት ለልባችሁ የቀረላችሁ ነገር ወይንም ጌታ ያስተማራችሁ ምንድነው?

______________________________________________________________________________

## ጥናት ሁለት

የንባብ ክፍል ከቁ 1-7
ርዕስ፡ የቅዱሳንን ልብ የሚያሳርፍ ህይወትና አገልግሎት

**ዓላማ፡-**

በክርስቶስ የዳነ ሰው በህይወቱም ሆነ በአገልግሎቱ የእግዚአብሔርን ህዝብ ልብ የሚያሳርፍ ሊሆን እንደሚገባው ለማሳሰብ ።

***መግቢያ፡-***

በዚህ አጭር መልዕክት ከቁጥር 1 እስከ ቁጥር 7 ባለው ክፍል ውስጥ ሐዋርያው ጳውሎስ እጅግ ጠቃሚ የሆነ ትምህርት ያስተምራል። ማንም ሰው በጌታ ከዳነ በኃላ በህይወቱም ሆነ በአገልግሎቱ የቅዱሳንን ልብ ማሳረፍ አንዱ የክርስትና ስነ ምግባር መሆን ስላለበት በፊልሞና ህይወት ያየውን መልካም ክርስቲያናዊ የስነ ምግባር ምሳሌ በመጥቀስ በዚህ ወንድም የህይወት ፍሬ ልቡ እንዳረፈ በመደጋገም ሲጠቅሰው እንመለከታለን፡፡ ይህንንም ዘላለማዊ የህይወት መርህ ሁላችንም ሥራ ላይ ማዋል እንዳለብን ያስተምራል።

### ሐዋርያው ጳውሎስ ለቅዱሳን የሚሰጠው ስፍራ (ቁጥ 1-3)

**ከቁጥር 1-3** ሐዋርያው ጳውሎስ አብረውት ስለሚያገለግሉትም ሆነ በአንድ ወቅት ያያቸውን አልያም ስለ እነርሱ በዝና ብቻ ስለ ሰማቸው ቅዱሳን ወንድሞችና እህቶች፡ የሚሰጣቸውን ከፍተኛ ግምትና ግንኙነቶች፡ ለማሳየት እንደ አባት ከጢሞቴዎስ ጋራ በተለያዩ ሥፍራዎች ልጄ ጢሞቴዎስ ሆይ እያለ ሲጽፍለት በዚህ ስፍራ ደግሞ ፊልሞናን በጌታ የተወደደ ወንድም አድርጎ ሲጠቅሰው እንመለከታለን። እንዲሁም “ለተወዳጁና አብሮን ለሚሰራው ፊልሞና” በማለት፡ በወንጌል ስራ አብረው ተካፋዮች ከመሆናቸውም በላይ በመካከላቸው ፍቅር መዋደድ እና በአገልግሎትም መቀባበል እንዳለ የሚያመለክት ክፍል ነው። እንዲሁም “እህታችን አፍቢያ” በማለት በጾታም ሆነ በየትኛውም መለኪያ ሰዎችን በክርስቶስ ካወቀበት ጊዜ አንስቶ የሚሰጠው ስፍራ የከበረ እና የላቀ እንደሆነ ያሳየናል። እንዲህ አይነቱ አቀራረብ የሐዋርያው የመግባቢያ ዘይቤ መሆኑን በየመልዕክታቱ ውስጥ ከሚጠቅሳቸውና ከሚያነሳቸው ወንድሞችና እህቶች ማየት እንችላለን (ሮሜ 16)። ሁላችንም በጌታ አንድ ቤተሰብ ነን። ሰውን ከልብ ወንድሜ ወይም እህቴ ብሎ መጥራት በአማኞች ልብ ውስጥ የተለየ የፍቅር ስሜት ይፈጥራል።

ሐዋርያው ጳውሎስ በሌሎች መልዕክቶች እንደሚጠቀመው ሁሉ መንፈሳዊ ሰላምታውን በቁጥር 3 ላይ ያቀርባል (ገላ1፡3 ኤፌ1፡2 ተመልከቱ)።ይህም የመልክቶቹ የአጻጻፍ ዘይቤ ቅደም ተከትል ነው (ማለትም ዘይቤውም ጸሐፊ፣ተቀባይ፣ሰላምታ፣ ምስጋና ወይም ጸሎት፣ዋናው መልዕክት ወይም ትንታኔ እና ቡራኬ ናቸው)።

### ለቅዱሳን ያለን ፍቅር እና በጌታ ላይ ያለን እምነት የሚሰማ እና የሚታይ ነው (ቁጥ 4-5)

**ከቁጥር4-5 በዚህ ክፍል መሰረት** ሐዋርያው ስለ ፊልሞና ከሰማው መልካም ዜና የተነሳ እግዚአብሔርን የሚያመሰግንበት ወይም በጸሎት ወደ እግዚአብሔር የሚቀርብበት ምክንያት ሆኖለታል። በዚህም ምክንያት በጸሎቱ አምላኩን ስለ ፊልሞና ከማመስገንም አልፎ እግዚአብሔር ከዚህ የበለጠ እንዲባርከውና የብዙ ወገኖችን ልብ የሚያሳርፍ እንዲሆን እና እግዚአብሔርም ከክፉ እንዲጠብቀው ጭምር ሊጸልይለት እንደሚችል ማሰብ ይቻላል። ለዚሁም የሐዋርያው ህይውት በሌሎች ክፍሎች ውስጥ ከሚያቀርባቸው ጸሎት አንጻር ይህንን እንደሚያደርግ ጥርጥር አይኖረውም። እንደ አዲስ ኪዳን ካህናት ሰዎችን በጌታ ዙፋን ፊት ይዘን መቅረብ የአገልግሎታችን አንዱ ክፍል ነው።

**ፍቅራችንና እምነታችን በተግባር የተገለጸ እና የሚታይ ይሁን (ቁ.6)**

በዚህ ቁጥር የሐዋርያውን አገላለጽ ስንመለከት ለቅዱሳን ወንድሞች የሚኖረንን ፍቅርም ሆነ በጌታ በኢየሱስ ላይ ያለን እምነት ሊታይና ሊሰማ የሚችሉባቸው መንገዶች ብዙ ቢሆኑም በሥራ ወይንም በተግባር የሚገለጽ እምነትም ሆነ ፍቅር ከብዙ ማስታወቂያ ወይንም የቃላት ድርደራ ይልቅ ጉልበት ያለው መሆኑን ያመለክታል። ተግባር ከእምነት የመነጨ መታዘዝና ፍቅር ሲሆን የበለጠ ጉልበት ይኖረዋል። ክርስቶስም ፍቅሩን በተግባር ገልጿል።
በተጨማሪም ይህ ቁጥር እንደሚያመለክተን እነ ሐዋርያው ጳውሎስ የሚያምኑት ዓይነት እምነት በፊልሞና ዘንድ ካለ ይህ እምነት በእነርሱ ህይወት ፍሬ የሚያፈራ ስለሆነ በፊልሞናም ዘንድ ያለው እምነት ፍሬ እንዲያፈራ ያስገነዝባል። ይህም ስለ እምነታቸው አንድነት ምስክር ይሆናል። በክርስቶስ የተገኘውን መንፈሳዊ አንድነት ከቅዱሳንም ጋር ስለሚካፈለው መልካም ህብረት በማሳሰብ እምነቱን በተግባር ለሌሎች ለማካፈል ይበልጥ እንዲተጋ ያሳስበዋል፤ያበረታተዋል። ይህንንም በማድረግ አንድ የዳነ ሰው የህይወት ግቡ ሊሆን የሚገባው እምነቱን ለሌሎች በማካፈል ለክርስቶስ ኢየሱስ ፍሬ በማፍራት ነው። **አንድ አይነት እምነት የተካፈልን ከሆነ ፍሬ ልናፈራ የግድ ነው (መንፈዊ ህብረታችን ፍሬ የሚያፈራ ሊሆን ይገባል)።**

**ክርስትና በፍቅር ህይወት የቅዱሳንን ልብ ማሳረፍ ነው (ቁ.7)**

**ቁጥር 7** ሐዋርያው ጳውሎስ የፊልሞና የእምነት እና የፍቅር ህይወት በዙሪያው ያሉትን ወንድሞችና እህቶችን ልብ በማሳረፉ ምክንያት ለሐዋርያው ለራሱ የተደረገለት ያህል በመቁጠር መጽናናት እንደሆነለት እና እንደተደሰተ ግልጽ ነው። በማቴ 10፡ 42 ጌታም ከእነዚህ መካከል ለአንዱ በስሜ ቀዝቃዛ ውሃ ብታጠጡ ለእኔ እንዳደረጋችሁት እቆጥራለሁ ያለውን ክፍል ማሰብ እንችላለን። እንግዲህ ልብ ማሳረፍ የሚቻለው በጌታ ላይ ያለንን እምነትና መደገፋችንን ለቅዱሳንም ያለንን መውደድና እና ፍቅር በተግባር በመግለጽ ብቻ ነው። ያዕቆብም በመልዕክቱ ሌሎችን መርዳት እግዚአብሔርን ማምለክ እንደሆነ ይናገራል (ያዕ1፡26-27)። አንድ ክርስቲያን እራሱን መጠየቅ ያለበት "በውጪ ያሉት ስለ እኔ ምን ይላሉ?" የሚል ጥያቄ ነው። ጌታም ስለ ራሱ ይህን ጥያቄ ጠይቋል (ማቴ 16፡13-14)። የሌሎችን ልብ የሚያሳርፍ የሚያስደስትና የሚያጽናና ህይወት እንድንኖር ተጠርተናል።

***መደምደሚያ***

አማኝ የተጠራው ወደ አንድ ቤተሰብ ነው። ይህንን ሀሳብ የፊልሞና መልእክት የመጀመሪያዎቹ ቁጥሮች ያመለክታሉ። በሐዋሪያው ጳውሎስ መልዕክት ብቻ "ወንድሞች ወይም ወንድም" የሚል ቃል ከ75 ጊዜ በላይ ተጠቅሶ ይገኛል። እርስ በእርስ ያለንን ፍቅር እና ህብረት ሌሎች ተመልክተው የአንድ አባት ልጆች መሆናችን በእነርሱ ዘንድ የተገለጠ ሊሆን ይገባል። ህይወታችንም በዚህ ቤተሰባዊ ፍቅር የተመሰከረ መሆን አለበት።

***የመወያያ ጥያቄዎች***

1. ከቁጥር 1 - 3 ባለው የሰላምታ ክፍል ሐዋርያው የሰዎችን ስም ለመጥቀስ የተጠቀመባቸውን ቃላት በመመልከት ስለ ሰዎቹ ህይወት ወይንም ባህሪያት ተወያዩበት? ከአጻጻፉስ ዘይቤ ምን እንማራለን?

---

2. በቁጥር 4- 5 መሰረት ለጌታ ለኢየሱስ እና ለቅዱሳን የሚኖረን ፍቅር እና እምነት እንዴት ነው ሊታወቅና ሊሰማ የሚችለው? (ሐዋርያው ጳውሎስ ይኽን ከሰማሁበት ቀን ጀምሮ በጸሎቴ እያሳሰብሁ ሁል ጊዜ አምላኬን አመሰግናለሁ ሲል ምን ማለቱ ነው ?

______________________________________________

3. በቁጥር 6 መሰረት የሐዋርያውን ጸሎት ዓላማ እንዴት ትረዳዋለህ ? በዚህ መሰረት የዳነ ሰው የህይወቱ ዓላምና ግብ መሆን ያለበት ምንድነው?

______________________________________________

4. በቁጥር 7 መሰረት ሐዋርያው ጳውሎስ ብዙ መጽናናት እና ደስታ ሊያገኝ የቻለው በማን እና በምን ምክንያት ነው? ከዚህስ ምን እንማራለን?

______________________________________________

5. የሰውን ልብ ማሳረፍ የሚለውን ሃስብ እንዴት ትረዱታላችሁ? ይህንንስ መሆን የሚቻለውስ እንዴት ነው?

______________________________________________

ሀ. ሰው በጌታ አምኖ ከዳነ በኃላ ከሌሎች ቅዱሳን ጋር ሊኖረው ስለሚገባ ግኑኝነትና የፍቅር ህወይት ከዛሬ ጥናት የተረዳኸውንአካፍል?

______________________________________________

ለ. ይህስ ሁላችንም ልንከተለውና የሚገባ እውነት ነው ወይንስ ከጥቂቶች ብቻ የሚጠበቅ ህይወት ነው ትላለህ? ለምን?

______________________________________________

ሐ. የቅዱሳንን ልብ ከማሳረፍ ህይወት ጎድለን ብንገኝስ ችግሩ ማን ጋር ያለ ይመስልሃል? ማስተካከያውስ ምንድነው ትላለህ

______________________________________________

መ. በዚህ ዙሪያ ህይወታችንን በመፈተሽ ጉድለት ቢኖርብን በእምነት ወደ ጌታ ጸጋ ዙፋን ፊት በጸሎት እንቅረብ።

______________________________________________

## ጥናት ሦስት

የንባብ ክፍል ቁጥር 8-15
ርዕስ
የማስታረቅ አገልግሎት

**ዓላማ፡-**

ክርስቲያን በጌታ ከዳነ ህይወቱ በምህረትና በይቅርታ የተሞላ ከመሆኑም አልፎ ሰዎችን ከእግዚአብሔር እና ከባልጀሮቻቸው ጋር የማስታረቅ አደራና አገልግሎት እንዳለበት ለማሳሰብ ነው።

***መግቢያ***

በአንድ ወቅት ከእግዚአብሔርም ሆነ ከወዳጆቻችን ጋር በጠላትነት የተጎዘንባቸው ጎዳናዎች መኖራቸው ባይካድም ከእግዚአብሔር ትልቅ ምህረትና ከጌታችን ከኢየሱስ የማስታረቅ አግልግሎት የተነሳ፡ ከእግዚአብሔርም ሆነ ከባልጀሮቻችን ጋር የሰላምን መንገድ እንድንከተል አብቅቶናል። ይህንን በምናስብበት ጊዜ ሁሉ የተቀበልነውን የመታረቅ ጸጋና የማስታረቅ አገልጎሎት በትጋት ለመወጣት ሊያነሳሳን ይገባል።ይህ ጥናት በዚህ ሃሳብ ዙሪያ የሚያተኩር ይሆናል።

**መንፈሳዊ ስልጣን እና ትህትና (ቁ.8-9)**

ቁጥር 8-9ከቁጥር 7 ጋር የተያያዘ ሃሳብ እንዳለው መዘንጋት የለብንም።- ምንም እንኳን ሐዋሪያው ጳውሎስ የሚያገለግላቸውን የማዘዝ መንፈሳዊ ሥልጣን ቢኖረውም በዓለም እንዳለው የአዛዥና የታዛዥነት ሥርዓት አይጠቀምም ወይም አይከተልም። የጌታም ቃል በዕብራውያንና በ1ጴጥ መልዕክት እንደሚከተለው ይላል "የእግዚአብሔርን ቃል የተናገሩአችሁን ዋኖቻችሁን አስቡ፥የኑሮአቸውን ምፍሬ እየተመለከታችሁ በእምነታቸው ምሰሉአቸው። .... ለዋኖቻችሁ ታዘዙና ተገዙ፤እነርሱ ስሌትን እንደሚሰጡ አድርገው፥ ይህንኑ በደስታ እንጂ በኃዘን እንዳያደርጉት፥ይህ የማይጠቅማችሁ ነበርና፥ ስለነፍሳችሁ ይተጋሉ" (ዕብ 13፡7 እና 17)።"እንዲሁም፥ ጒበዞች ሆይ፥ ለሽማግሌዎች ተገዙ፤ሁላችሁም እርስበርሳችሁ እየተዋረዳችሁ ትሕትናን እንደ ልብስ ታጠቁ፥ እግዚአብሔር ትዕቢተኞችን ይቃወማልና፥ለትሑታን ግን ጸጋን ይሰጣል"(1ጴጥ 5፥5)።

በሌሎች ክፍሎች ላይ እኛ መንፈሳዊውን ነገር ካካፈልናችሁ ከእናንተ ደግሞ በአጸፌታው ሥጋዊውን በረከት ልናጭድ መብት አለኝ ሲላቸው (1ጢሞን5፡18፤2ቆሮ 9፡9)፡ እንዲሁም የሚያበራየውን በሬ አፉን አትያዘው በማለት ለሰራተኛ ደመወዙ የተገባው እንደ ሆነ ሁሉ እንዲሁ እርሱ አገልጋይ የጌታም ሐዋሪያ ከመሆኑ አንጻር እንኳን ብቻ ቢታይ ፊልሞናን ለማዘዝ የሚያበቃ መብት ወይም ድፍረት እንዳለው መገንዘብ ይቻላል። እንግዲህ ይህ የማዘዝ መብቱ የተጠበቀ ቢሆንም ሐዋርያው ከዚህ ይልቅ ትህትና በሞላበት መልኩ ልመናን ማቅረብን እንደመረጠ ማየት ይቻላል። በዚህም አያይዞ ለፊልሞና ለሚያቀርበው ልመና ክብደት ለመስጠት እንዲያስችለው በእድሜም ካስፈለገ ታላቅ መሆኑን እና በህይወቱም ያለበትንም ሁኔታ በመጥቀስ ማለትም በወንጀል ሳይሆን በጌታ ወንጌል ምክንያት እስረኛ መሆኑን ሲገልጽ እንመለከታለን። በሌላ አባባል ሐዋርያው ለጌታ ወንጌል እራሱን ለእስርና ለሞት እንኳን የሰጠ ከሆነ ፊልሞናም የተበደለው በደልንና የጠፋበትን ንብረት ሰውን ለማዳንና ለጌታ ክብር እንዲተው ይገባዋል የሚለውን ሃሳብ የሚጠቁም መልዕክት ነው።

**የበደሉንን ልንቀበል ይገባል 10-13ሀ**

ከዚህ በመቀጠል ሐዋርያው ጳውሎስ የመልዕክቱ ዋና የሆነው የእርቅ ጉዳይ <u>**በቁጥር 10 እና 11**</u> ላይ ይጠቅሳል። ሐዋርያው ጳውሎስ እጅግ በጣም አስተዋይ እና ጥበበኛ አገልጋይ መሆኑን ይበልጥ እናያለን። ምክንያቱም እስከዚህ ቁጥር ድረስ የእርቁን ጉዳይ ሳያነሳ፡ በተለያዩ የማግባቢያና የማለዘቢያ ሃሳቦች የፊሊሞናን ልብና ሃሳብ ሲያግባባና ሲያዘጋጅ እናያለን። በመቀጠልም አስቀድሞ ምንም እንኳን አገልጋዩ አናሲሞስ ፊልሞናን የበደለውና የጎዳው ቢሆንም አሁን የተለወጠ ወንድም በመሆኑ በይቅርታ እንዲቀበለው በቀጥታ ይማጸነዋል። ይህም የሰውን ድካምና ማንነት ባለፈ መልኩ ሌሎችን በተለይም የበደለውን በጌታ እንደ ወንድም አድርጎ እንዲቀበለው ያሳስበዋል። **ቁጥር 11-12** ሐዋርያው ፍልሞና አናሲሞስን በርህራሄና በምህረት እንዲቀበለው ሲጠይቀው ጳውሎስ ያለፈውን የራሱን ህይወት ታሪክ እንዴት በአመጽና በበደል ጎዳና ሲሄድ ጌታ በምህረቱ እንደተገናኘውና ስሙን ለመሸከም የተመረጠ እቃው እንዳደረገ ባለመዘንጋት መሆኑ ግልጽ ነው (1ጢሞ 2፡7)። እርሱም ሌሎችን ለመቀበል ይህ ጉልበት እና አቅም እንደሚሰጠው ማሰብ ይቻላል።

ቁጥር 11-13 ጳውሎስ አናሲሞስ የፈጸመውን በደል አልደበቀም።እንዲሁም ከዚህ በኃላም ከዚህ ቀደም የፈጸመውን በደል የማያደርግ አዲስ ሰው የሚጠቅምና የተወደደ መሆኑንን በመግለጽ ፊልሞና እንዲቀበለው ሲያግባባው እንመለከታለን። በአንድ ወቅት ሐዋሪያው ጳውሎስም ከማርቆስ ጋር እስኪለያዩ ድረስ መከፋፋት በመካከላቸው የተፈጠረ ቢሆንም በመጨረሻ ሐዋርያው ጳውሎስ ማርቆስን በይቅርታ ተቀብሎት እንደ ገና ለአገልግሎት እንደሚጠቅመው በመረዳት እንዲመጣለት እንደጠየቀ ህይወቱን መመስከር ይቻላል ( ሐዋ 15፡39, ቆላ፡10-11 2ጢሞ4፡11 እና ፊል፡24)። ወንጌል የሰላምና የእርቅ መንገድ ስለሆነ የበደሉንና ያሳዘኑንን ሰዎች (ጠላቶቻችን ናቸው ብለን የፈረጅናቸውን ) ቢሆኑም በይቅርታ ብንቀበላቸው ለእኛም የሚጠቅሙን በጌታም የተወደዱ ወንድሞችና እህቶች ሊሆኑ ይችላሉ።

ቁጥር 14 በቁጥር 8 እና 9 ላይ ያለውን ሃሳብ የሚያጠናክር ይሆናል። ቁጥር 15 ግን ይህ ግኑኝነት ጊዜያዊ ሳይሆን ዘላቂና ዘላለማዊ መሆኑን ትክሩት የሚሰጥ ሃሳብ ነው።

***መደምደሚያ***

የመጽሐፍ ቅዱስ ማዕከላዊ መልዕክት ድነት ነው። ይህም ማለት ሰዎችን ከእግዚአብሔር ጋር ማስተረቅ ነው። ከጌታ ጋር የታረቀ ሰው ሰዎችን ከሰዎች ጋር ያስታርቃል (2ቆሮ 5፡15-18)። ጌታ በደላችንና ኃጢአታችንን እንደተወ ሙሉ በሙሉ ሌሎችን ይቅር ማለት አለብን። የታረቀ ሰው ደግሞ ለጌታም ይሁን ለሰዎች ይጠቅማል። ሰዎችን የማስታረቅ መንፈሳዊ ሥልጣን እንዳለን መገንዘብ አለብን። ይቅር ያላለ ሰው ጸሎቱ ሙላት አይኖረውም። እንደገና ሰዎችን እንቀበላቸው።

## ***የመወያያ ጥያቄዎች***

1. ከቁጥር 8-9 መሰረት ሐዋርያው ጳውሎስ ፊልሞናን በጌታ የማዘዝ ድፍረት እንዳለው ይጠቅሳል፡፡ የጌታም ቃል በዕብራውያንና በ1ጴጥሮስ መልዕክት ይህንን ሀሳብ ይደግፋል (ዕብ 13፡7 እና 17፣1ጴጥ 5፥5)።ይህን በራሳችሁ አባበል እንዴት ትገልጹታላችሁ?

___

2. ነገር ግን በቁጥር 8 እና 9 ከማዘዝ ይልቅ በፍቅር እለምንሃለው ማለቱስ ከላይኛው ጥያቄ ጋር ልዩነቱ ምንድ ነው ትላላችሁ? ሥልጣኑንስ የተጠቀመው እንዴት ነው?

___

3. በዚሁ ክፍል "እኔ ጳውሎስ ሽማግሌው የክርስቶም እስር የሆንኩ" የሚሉትን ቃላትና ሀረጎች መጠቀም የመረጠበት ምክንያት ለምንድነው ትላለህ?

---

4. እስከ ቁጥር 10 ሐዋርያው ጳውሎስ መልዕክቱን የጻፈበትን ዋና የሆነውን ነገር የአናሲሞስን ጉዳይ ለፊልሞና ያላነሳበት ምክንያት ምን ይመስልሃል?

---

5. ከቁጥር 10-12 መሰረት ሐዋርያው ጳውሎስ ስለኮብላዩ እና ጌታውን ስለበደለወ አናሲሞስ ያለው አስተሳሰብ እንዴት ትመለከተዋለህ? እንዲህስ እንዲያስብ ያደረገው ምንድነው ብለህ ታስባለህ?

---

6. በቁ.11-15 ሐዋርያው ጳውሎስ ፊልሞና ስለ አናሲሞስ ያለውን አስተሳሰብ እንዲቀይር ያግባባው በእንዴት አይነት መንገድ ነው?

---

7. የሐዋርያው ጳውሎስ የቀደመው ህይወትና ከጌታ ምህረት ማግኘቱ ለዚህ የማስታረቅ አገልግሎት አስተዋጾ ያደረገ ይመስልሃል ? እንዴት?( 1 ጢሞ 1፡ 13 ይመ. ኤፌ 4፡32, ቆላ 3፡13)።

---

8. አንተስ የበደሉህን ሰዎች ይቅር ብለህ የተቀበልክበት ጊዜ ይኖራል ? በዚህ መሰረት አሁንስ የበደሉህ ካሉ ምን ልታደርግ ይገባሃል?

---

## ጥናት አራት

የንባብ ክፍል ከቁጥር 16-25
ርዕስ፡-የበደሉንን በመቀብል በይቅርታ ህይወት መመላለስ (ለአገልግሎት ማብቃት)

**ዓላማ**

ከሰዎች ጋር ባለን ግኑኝነት የምንጋጭባቸውና የምንለያይባቸው ጊዚያት መኖራቸው ስለማይቀር ጌታ ሃጢያቱን ያልቆጠረበት ሰው የሌሎችን በደልና መተላለፍ በይቅርታና በምህረት እያለፈ መኖር እንዳለበት ለማስገንዘብ ነው።

**መግቢያ**

ከሰዎች ጋር አብረን ስንኖርና ስናገለግል መጋጨትም ሆነ በሃሳብ መለያየት ሊኖር እንደሚችል ሊካድ የማይቻል ስለሆነ በእንደዚህ አይነት ጊዜ ክርስቲያን ሊያስተውለውና ሊገነዘበው የሚገባው እርሱ ከጌታ የተቀበለውን ምህረት በማሰብ የሌሎችን በደልና መተላለፍ በይቅርታ እያለፈ ለበደሉት ዳግመኛ እድልን እየሰጠ ከቅዱሳን ጋር ያለውን ህብረትና ፍቅር መንከባከብ ክርቲያናዊ ተግባሩ ሊሆን ይገባል። ይህም በይቅርታ የተቀበልናቸው ወገኖች ወደ አገልጋዮች እስኪሆኑ ድረስ እድል ሊሰጣቸው ይችላል።

**ይቅር ያልናቸውን ተቀብለን ዳግመኛ እድል ልንሰጣቸው ይገባል(ቁ.16-17**)

**ቁጥር 16-17** ሐዋሪያው ጳውሎስ ፊልሞናን ከዚህ በፊት በድሎና አጥፍቶ የተለየውን አናሲሞስን ከዚህ በኃላ እንደ ቀደመው ማንነት ሳይሆን ከበፊቱ የላቀና የተሻለ ስፍራ እዲሰጠውና እንደ ባሪያ ሳይሆን እንደ ተወደደ ወንድም እንዲቀበለው ሲማጸን እናያለን። ጊዜያዊ ግጭቶችና ችግሮች ዘለቄታ ያለውን ወዳጅነትንና ወድማማችንነት በተለይም በጌታ ያለንን ህብረት ማለትም ዘለዓለማዊውን ነገር ሊነካብን እንደሚችል መዘንጋት የለብንም። በጳውሎስ እምነትና የህይወት ተመክሮ መሰረት አንድ ሰው በምንም ሁኔታ ባደረገው ነገር አዝኖና ተጸጽቶ ከክፉ መንገዱ ቢመለስ ዳግመኛ እድል ሊሰጠው እንደሚገባ ያምናል።ምክንያቱም እርሱ እራሱ እግዚአብሔር ከሓጢያተኞች ዋነኛ በሚሆን ሰው ላይ ምህረቱን እንዴት እንደገለጠ በህይወቱ አይቶታል። ስለዚህ ጳውሎስ ሰዎች ሁለተኛ እድል እንዲሰጣቸው ብቻ ሳይሆን እግዚአብሔር የሰዎችን ህይወት እንደሚለውጥ የሚያምንም ሰው ስለሆነ አሁን የሚያየው በጌታ የታደሰውን አዲሱን አናሲሞስን ስለሆነ እንደ ተወደደ ወንድም እንዲቀበለው ያሳሰበዋል። ስለዚህ በሰዎች ላይ አንድ ጊዜ ያየነውን ጉድለትና ጥፋት ብቻ እያሰብን ሁል ጊዜም ሰዎቹ እንደዛው ሳይለውጡ እንደሚኖሩ ልናስብ አይገባንም። ይልቁንም አዲስ ምዕራፍን በሰው ህይወት ውስጥ መጀመር የሚችለውን ጌታ በራሳችን ህይወት እና ተመክሮ ስላየነው ሌሎችንም ለመቀበል ልባችን ሰፊና ክፍት ሊሆን የግድ ነው። ለዚህ ጥሩ ምሳሌ ሊሆንልን የሚችለው ጌታ ኢየሱስ በሐዋሪያው ጴጥሮስ ድካምም ሆነ በደል ተስፋ ሳይቆርጥ የአገልግሎት አደራና ሹመት ለመቀበል እዲችል አብቅቶታል (ዮሐ21፡15-17)።ማቴ 18፡22 እንደሚነግረን ይቅርታ ማቆሚያ የለውም። በጥቅሉ ፍቅር ማሸነፍ አለበት።

**ሌሎችን ወደ ቀደመው ሥፍራና አገልግሎት መመለስ ዋጋ ያስከፍላል ቁ. 18-19**

ሐዋርያው ጳውሎስ ስለ አናሲሞስ እርግጠኛ ሆኖ ከሚናገርው በመነሳት በአናሲሞስ ህይወት ውስጥ እውነተኛ መለወጥ እና በጌታ መነካት እንደተካሄደ ማሰብ ይቻላል፡ በተጨማሪም አናሲሞስ በበዳዩ ፊት መልሶ ለእርቅ ለመቆም መዘጋጀቱ የህይወቱን ትክክለኛ መለወጥን የሚያመልክት ይሆናል። እንዲሁም ሐዋርያው ጳውሎስ በፊልሞና እና በአናሲሞስ መካከል እውነተኛ እርቅ በማድረግ ከዚህ በፊት የነበራቸውን ህብረት ማደስ ብቻ ሳይሆን ከዚህ በኃላ ከበፊቱ በተሻለ እና በበለጠ

መልኩ ሊቀባበሉ እንደሚገባ ያሳስባቸዋል። ሐዋሪያው ጳውሎስ ለአናሲሞስ ህይወትና አገልግሎት መብቃት መክፈል የሚገባውን ዋጋ ሁሉ ለመክፈል ቃል ሲገባ እናያለን። ጳውሎስ የእነዚህን ሁለት ሰዎች እርቅ በተመለከተ የሚያስከፍለውን ዋጋ በተለይም አናሲሞስ አጥፍቶ የነበረውን ቁሳቁስ ከዚህ በኃላ ካስፈለገ ጳውሎስ ለመክፈል ዝግጁ በመሆን "በእኔ ላይ ቁጠረው" ይላል። ጌታም የሁላችንን በደል ተሸክሞ ስለእኛ እንደ ተቀጣ የሚያስስብ ክፍል ነው። ቅጣታችንን የተቀጣልንና አበሳችንን ከእኛ ያራቀል ጌታ ስሙ ይባረክ ። እኛም ዛሬ እርሱ ይቅር እንዳለን እርስ በእርሳችንን ይቅር ልንባባልም ሆነ ሌሎችንም ከእግዚአብሔርም ሆነ ከባልጀሮቻቸው ጋር ለማስታረቅ አደራ እንዳለብን ልንዘነጋው ፈጽሞ የማይገባ ጉዳይ ነው።

**በጌታ ሌሎችን ለቁም ነገር የማብቃት ደስታ (እርካታ) ቁ. 20-21**

ሐዋርያው ጳውሎስ የጌታ መንፈስ ረድቶት የእርቁን ጉዳይ ድምዳሞ ላይ ለማድረስና ለማጠቃለል እየጣረ መሆኑን እናያለን። ሐዋርያው ጳውሎስ ለፊልሞና ያቀረበውን የእርቅ ልመና አወንታዊ ምላሽ እንደሚያገኝ እርግጠኛ መሆኑንን በግልጽ የሚያመለክት ሃስብ ነው። ይህም ለሐዋርያው ጳውሎስ ጥቅሙ ነው (ማለትም የልብ ደስታና በረከት) ነው። ቅዱሳንን ወንድሞች እና አገልጋዮችን በመታዘዝ ልባቸውን በማሳረፍ በረከት ልንሆናቸው እንችላለን። ለምሳሌ አንድ ሰው ለጌታ ብሎ መልካም እና በጎ ነገር ቢያደርግ በቅዱሳን መካከል ደስታ መፈጠር ምክንያት እንደሚሆን ሁሉ ጳውሎስም እየገለጸ ያለው ተመሳሳይ ሃሳብ ነው።

**ክርስቲያናዊ ግንኙነቶች በጥበብና እርስ በእርስ በመተማመን መያዝ አለበት ቁጥር 22-25**

ሐዋርያው ጳውሎስ የእርቁ ጥያቄ ከፊልሞና አወንታዊ ምላሽ እንደሚያገኝ በማመን ወይንም እርግጠኛ በመሆን ወደ ፊት ሊጎበኛቸው ሲመጣ ማረፊያ እንዲያዘጋጅለት በማሳሰብ ይናገራል። በጉብኝቱም የእርቁን ውጤትና ዘላቂነት ለማየት እድል የሚኖረው እንደሆነ በማሳሰብ ለጉዳዩ ጫና እና ትኩረት እንዲሰጥ ሲያደርገው ይታያል ። ብዙዎች ሐዋሪያው ከመጀመሪያው ዙር እስር ተፈትቶ ቆላስይስን እንደጎበኘ ይናገራሉ።

በተጨማሪም ከሐዋሪያው ጋር አብረው ያሉ አገልጋዮችም የከበረ ሰላምታ በማቅረባቸው ምክንያት ጉዳዩ ተጨማሪ ክብደት እንዲሰጠው ያደርጋል። እንዲህ አይነቱ አካሄድ ከአንድ የጌታ ባሪያና አገልጋይ ሊኖረው የሚገባ ጥበብና ማስተወል ስለሆነ ይህ አቀራረብ ሰዎችን ለእርቅ የሚያዘጋጅ እንደሆነ ማየት አይከብድም።

***መደምደሚያ***

ጌታ ብዙዎችን ይቅር ብሏቸው ሰው አድርጓቸዋል። እግዚአብሔርም ትዕግስቱ ብዙ ነው። በሐዋርያው ጳውሎስ ጥልቅ መንፈሳዊ እውቀት በሞላበት አገልግሎት እነዚህ ሁለቱ ሰዎች ለቁም ነገር በቅቷል። በመግቢያው እንደተጠቀሰው አናሲሞስም ሆነ ፊልሞና በቆላስያስ አካባቢ በሚገኙ አብያተክርስቲያናት ውስጥ አገልጋዮች እንደነበሩ ከታሪክ ስለምንገነዘብ በሁለቱ መካከል የሰመረ እርቅ እንደተፈጠረ ያመለከታል። አናሲሞስ ከበደለኝነት ህይወት በመውጣት ለእርቅ በበደለው ሰው ፊት ለመቆም አቅም የሆነለት ከእግዚአብሔር የተቀበለው ምህረት ብቻ ነው። በትናንትናው ክፉ ህይወቱ ላይ በድል እንዲቆምና በነገው ስጋትና ፍርሃቱ ላይ በድፍረት እንዲውጣ ያበቃው የሰውን ልብና ህይወት የሚለውጠው የጌታ ጸጋ ብቻ ነው። በሉቃስ ወንጌል 15 የተጠቀሰው የጠፋው ልጅና የአባቱ ታሪክ ለዚህ ትልቅ ትምህርት ይሰጠናል። እኛም አማኞች ፈጹም የይቅርታና የመቀባበል ህይወት እንዲኖረን ይህ መልዕክት ያስተምረናል።

***የመወያያ ጥያቄዎች***

1. ከቁ 16- 17 መሰረት በድሎ ከቤት የኮበለለውን ባሪያውን ፊልሞና እንዴት እንዲቀበለው ነው የሚያሳስበው? በጊዜያዊ ግጭቶችና  አለመግባባቶች ምክንያት ሊፈጠር የሚችለው ጉዳት ምን ያህል የከፋ እንደሆነ ተነጋገሩበት። ዘለዓለማዊ የሆነውን ግንኙነታችንን ይጎዳልን?

2. ከቁጥር 16-17 አንድ ሰው የፈጸመው በደል ባይካድም እውነተኛ የህይወት ለውጥ ካሳየ ዳግመኛ ምን ሊሰጠው የሚያስፈልግ ይመስልሃል? ለምን ? በዚህ ዙሪያ ከሐዋርያው ጴጥሮስ የህይወት ታሪክ የምንማረው ነገር ይኖራል?

3. በቁጥር 16 መሰረት ከአናሲሞስ ታሪክ በመነሳት ሰዎች በአንድ ወቅት የበደሉንን ብቻ ሁሌም ማሰብ የሌለብን ለምን ይመስልሃል? ለአንተማ በሥጋም በጌታም የተወደደ ከባሪያ የሚሻል ወንድም እንዴት አይሆንህም ማለቱን እንዴት ትረደዋለህ ?

4. ከቁጥር 16-18 በአናሲሞስ ህይወት ውስጥ የተካሄደው ለውጥ መኖሩን የሚያመለክት ነገር ምንድነው?

5. ከቁ. 15- 17 በአንድ ወቅት ከበደሉን ሰዎች ጋር እውነተኛ እርቅ ካደረግን ለሰዎቹ የምንሰጣቸው ስፍራ ምን ሊሆን ይገባል ትላለህ?

*ለጥናቱ የተመደበው ጊዜ ያልበቃችሁ ከሆነ ከዚህ ቀጥሎ ያለውን ለሚቀጥለው የጥናት ጊዜ ማስተላለፍ ትችላላችሁ*

6. ከቁጥር 18-19 መሰረት ሐዋርያው ጳውሎስ ፊልሞናን እና አናሲሞስን ለማስታረቅ ምን ድረስ እንደ ሄደ ተወያዩበት ?(በእኔ ላይ ቁጠረው)ይህስ ከወንጌል የማስታረቅ አገልግሎት አንጻር እንዴት እንመለከታለን?2ቆሮ5፣17-18

7. ከዚህ ጥናት በመነሳት የቱንም አይነት ከባድ የሚመስል ጉዳይ በጥበብና በትህትና ከእውነት ጋር ሲቀርብ ምን ያህል ጉልበት እንዳለው አስተዋልክ? አዎን ካላችሁ በምን መልኩ ነው የቀረበው?

8. በዚህ ታሪክ መሰረት አናሲሞስ የትናንቱ በደል ሳይዘው ወደ ፊት ለመቀጠል ወደ ነገው ለመዘርጋት ጉልበት የሆነለት ምንድነው ትላላችሁ? ንጉስ ዳዊትን እግዚአብሔር እንዴት ይቅር እንዳለው ተወያዩ?

9. ከቁ. 22-25 በፊልሞና እና በሐዋርያው ጳውሎስ ቀጣይ ግኑኝነትም ሆነ የእርቁ ጉዳይ ድምዳሞዎ አመላካች ምንድነው?

10. ከዛሬው የጥናት ክፍል በይቅርታ ህይወት ስለመኖር እና የተበላሹብን ግኑኝነቶች ቢኖሩ በምህረት አድሰን በፍቅርና በቅዱሳን ህብረት ስለመኖር የቀረልህን ሃሳብ አጠር በማድረግ አካፍል?

______________________________________________________________________